## የፊልጵስዩስ መጽሐፍ መግቢያ

1. ፀሐፊው :- ሐዋርያው ጳውሎስ ነው::
   ፊሊ.1፡1-2 ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ጻፈው እንረዳለን በሌሎችም ቦታዎች ስለራሱ ጽፎአል ( ፊሊ 1፡12-24, ፊሊ 2፡19-24, ፊሊ 3:4-14, ፊሊ 4:10-16 )

2. የተጻፈው:- በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ አማኞች

3. የተጻፈበት ጊዜና ሁኔታ
   ሀ. ይህን መልዕክት ሲጻፍ በሮም በእስር ቤት ሆኖ ነው
   ፊሊ 1፡7, 13, 17
   ለ. ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልዕክት ሲጻፍ በሮም በእስር ቤት ሆኖ ለፍርድ እየተዘጋጀ ባለበት ሁኔታ ነው የጻፈው ::
   - የፍርዱ ውጤት መሞት ወይም ነፃ መለቀቅ እንደሚሆን ያውቅ ነበር
     ፊሊ 1፡19-20   ፊሊ 2፡17, 24
   ሐ. ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልዕክት በጻፈበት ጊዜ ጢሞቴዎስና አፍሮዲጡን አብረውት ነበሩ::

4. የቤተክርስቲያኒቱ አመሠራረት ሐዋርያ ስራ 16፡11-40

"ቅድስና ለእግዚአብሔር"
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

5. የተጻፈባቸው ዓላማዎች
   ሀ. ሐዋርያው ጳውሎስ ያለበትን ሁኔታና የወደፊት እቅዱን ሊገልጽላቸው
   ( ፊሊ 1፡12-26, ፊሊ 2፡24 )
   ለ. በተቃውሞና በመከራ መሐል በወንጌል ጸንተው እንዲቆሙ ለማበረታታት
   (ፊሊ 1:27-30 ፊሊ 2:18 ፊሊ 3:1 ፊሊ 4:4 )
   ሐ. በቤተክርስቲያን በአንድነት ተስማምተው እንዲኖሩ ለመምከር
   ( ፊሊ 1:27 ፊሊ 2:2-4, 16 ፊሊ 4: 1-2 )
   መ. እርሱን እንዲያገለግሉ ስለላኩት አገልጋይ ስለ አፍሮዲጡን ሊገልጽላቸው
   (ፊሊ 4:10-20 )
   ሠ. ከስህተት አስተማሪዎች እንዲጠነቀቁ ለማሳሰብ
   (ፊሊ 4፡10-20 )
   ረ. በልግስና ስለላኩለት ስጦታ ለማመስገን
   ( ፊሊ 4፡10-20 )

## ክፍል አንድ

ርዕስ ፡- ሰላምታና ምስጋና

መግቢያ፡- ሐዋርያ ጳውሎስ ለበፊልጵስዩስ ምዕመናን ያቀረበውን የናፍቆት ሠላምታና ስለእርሱ ወደ እግዚአብሔር ያቀረበውን ፀሎትና ምስጋና እንመለከታለን

ዓላማ፡- በወንጌል አገልግሎት በመሳተፍ በጽድቅ ኑሮ ለእግዚአብሔር ክብር መኖር እንደሚገባ ለመገንዘብ

### የጥናቱ ክፍል ፡- በፊልጵስዩስ 1፡1-11

" የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች የሆኑ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ ከኤጲስ ቆጶሳትና ከዲያቆናት ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ሁልጊዜ በጸሎቴ ሁሉ ስለ እናንተ ሁሉ በደስታ እየጸለይሁ ከፊተኛው ቀን እስከ ዛሬ ድረስ ወንጌልን በመስበክ አብራችሁ ስለ ሠራችሁ፥ ባሰብኋችሁ ጊዜ ሁሉ አምላኬን አመሰግናለሁ በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና በእስራቴም ወንጌልንም መመከቻና መጽኛ በማድረግ ሁላችሁ ከእኔ ጋር በጸጋ ተካፋዮች ስለ ሆናችሁ በልቤ ትኖራላችሁና ስለ ሁላችሁ ይህን ላስብ ይገባኛል በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር ሁላችሁን እንዴት እንድናፍቃችሁ እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና ለእግዚአብሔርም ክብርና ምስጋና ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝ የጽድቅ ፍሬ ሞልቶባችሁ ለክርስቶስ ቀን ተዘጋጅታችሁ ቅኖችና አለ ነውር እንድትሆኑ የሚሻለውን ነገር ፈትናችሁ ትወዱ ዘንድ ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህን እጸልያለሁ "

የመወያያ ጥያቄዎች :-

1. ሐዋርያው በመልክቶቹ ሁሉ ከአባታችን ከእግዚአብሔር ከጌታም ከእየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሠላም ለእናንተ ይሁን እያለ ይጽፋል።
   - በእነዚም ሰላምታዎች ሊያሳስበን የሚፈልገው ነገር አለ ? ወይስ የተለመደው ሰላምታ ስለሆነ ነው ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. ከቁጥር 3 እስከ 5 ስታነብ ሐዋያው ጳውሎስ የሚያመሰግነው ስለምንድን እንደሆነ ታስተውላለህ ?

3. ቁጥር 6 ስታነብ " በእናንተ መልካሙን ሥራ የጀመረው " ሲል ምን ማለቱ ነው?

- ይህ መልካም ሥራ መቼ ነው የሚፈጽመው? ከዚህስ ምን ትማራለህ?

4. ጳውሎስ ስለ ሁላችን ላስብ ይገባኛል ብሎ የሚሰጠው ምክንያት ምንድነው?

5. ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ምዕመናን የነበረው ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ ከክፍሉ ሃሳብ ትረዳለህ ? ( ቁጥር 8 )

6. ሐዋ. ጳውሎስ ስለምን እና ስለለምን ነው ለፊልጵስዩስ ሰዎች የሚፀልይላቸው?
- በዝርዝር ፃፋቸው እና ምን ማለት እንደሆነ በማብራራት ተወያይባቸው

7. ከፊልጵስዩስ ሰዎች ምዕመናን አገልግሎት ስትመለከት በቤተክርስቲያናችን ላለን አገልግሎት ምን የምንማረው ነገር አለ ብለህ ታስባለህ ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

8. ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች ከነበረው ፍቅርና ከፀለየው ፀሎት ለራስህም ሆነ ለሌሎች ሰዎች በምንና በምን ርዕስ መፀለይ እንደሚገባህ ተረዳህ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ማስታወሻ**

- ከዚህ ክፍል በተማርከው እና በተረዳኸው እውነት በመነሳት በእነዚህ ርዕሶች ላይ ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ፡፡
- በመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራም በዚህ ሳምንት ውስጥ ከውይት ተካፋዮችህ ጋር በመነጋገር አንዱ ለሌላው በዚህ የፀሎት ርዕስ ላይ እንዲፀልዩ አድርግ፡፡

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 1፡6**

**“ በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና ”**

## ክፍል ሁለት

ርዕስ :- የምሥራቹ ቃል በመሰበኩ የሚገኝ ደስታ

መግቢያ :- ሐዋርያ ጳውሎስ በመታሰሩ ምክንያት የምሥራቹ ቃል እንዳልታሰረና ለፊሊጲስዮስ ሰዎች የታሠረበትን ምክንያት በግልፅ በማስረዳት የፃፈውን እንመለከታለን::

ዓላማ :- የእኛ ትልቁ ደስታ ሊሆን የሚገባው በጌታ ወንጌል መስበክ ላይ መሆኑን ለማመልከትና ከራሳችን ምቾትና ስም በላይ የክርስቶስን ወንጌል ማስቀደም እንደሚገባን ለመረዳት::

**የጥናቱ ክፍል :- ፊሊጲስዮስ 1፥12-19**

“ ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ ስለዚህም እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንዲሆን በንጉሥ ዘበኞች ሁሉና በሌሎች ሁሉ ዘንድ ተገልጦአል በጌታም ካሉት ወንድሞች የሚበዙት ስለ እስራቴ ታምነው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲነግሩ ያለ ፍርሃት ከፊት ይልቅ ይደፍራሉ አንዳንዶች ከቅንአትና ከክርክር እንኳ ሌሎች ግን ከበጎ ፈቃድ የተነሣ ክርስቶስን ይሰብኩታል እነዚህ ወንጌልን መመከቻ ለማድረግ እንደ ተሾምሁ አውቀው በፍቅር ይሰብካሉ እነዚያ ግን በእስራቴ ላይ መከራን ሊያመጡብኝ መስሎአቸው ለወገናቸው የሚጠቅም ፈልገው በቅን አሳብ ሳይሆኑ ስለ ክርስቶስ ያወራሉ ምን አለ? ቢሆንም በሁሉ ጎዳና በማመካኘት ቢሆን ወይም በቅንነት ቢሆን ክርስቶስ ይሰበካል ስለዚህም ደስ ብሎኛል ወደ ፊትም ደግሞ ደስ ይለኛል፤ ይህ በጸሎታችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት ለመዳኔ እንዲሆንልኝ አውቃለሁና ”

የመወያያ ጥያቄዎች :-

1. በቁጥር 12-14 ባለው ውስጥ ሐዋ. ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች የሚነግራቸው ምንድነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ለምን ይህንን ለፊልጵስዩስ አመኞች መፃፍ ያስፈለገው ይመስልሃል?

ከቁጥር 15 - 17 ስለእነማን ነው ሐዋርያው ጳውሎስ የሚናገረው?

- ከ ቁ. 15–17 እና ከ ቁ.18-19 በሁለቱ ክፍል መካከል የተመለከትከው ልዩነት ምንድነው?

- ሐዋ. ጳውሎስ በ ቁጥር 18-19 "እደሰታለሁ" የሚለው በምንና በምን ነገሮች ነው?

2. ለሐዋርያው ጳውሎስ በቁጥር 19 ላይ " ለመዳኔ እንዲሆንልኝ አውቃለሁ " ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ትረዳለህ?

3. በሁሉ ጎዳና ክርስቶስ ይሰበካል ስለዚህ ደስ ይለኛል በማለቱ ከሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት ምን የምትማረው ነገር አለህ?

አንተስ ከቁጥር 15-18 ስታነብ በህይወትህ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ መናገር ትችላለህ?

4. የቁጥር 19 ሃሳብ አብራራ።

5. በክፍሉ ምንባብ መሠረት(ቁ.18-19) ያንተ፤ የእኛ የክርስቲያኖች ትልቁ ደስታ ሊሆን የሚገባው ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

6. አንተስ ከዚህ ክፍል ልትማረው እና ለህይወትህ ምን የቀረልህ እውነት አለ ? ይህንን የተማርከውን ለውይይት ተካፋዮችህ አብራርተህ በመግለጽ አካፍላቸው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**ማስታወሻ**

- ከዚህ ክፍል በተማርከው እና በተረዳኸው እውነት በመነሳት በእነዚህ ርዕሶች ላይ ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ፡፡

"ቅድስና ለእግዚአብሔር"

ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 1፡18**

**" በሁሉ ጎዳና በማመካኘት ቢሆን ወይም በቅንነት ቢሆን ክርስቶስ ይሰበካል ስለዚህም ደስ ብሎኛል "**

## ክፍል ሶስት

ርዕስ ፡- ጌታ እየሱስ ክርስቶስን የሚያከብር ሕይወት

መግቢያ ፡- ሐዋርያው ጳውሎስ እርሱ በመታሰሩ ምክንያት የምሥራቹ ቃል ግን እንዳልታሰረና ለፊሊጲስዮስ ሰዎች የታሠረበትን ምክንያት በግልፅ በማስረዳት የፃፈውን እንመለከታለን

ዓላማ ፡- የእኛ ትልቁ ደስታ ሊሆን የሚገባው በጌታ ወንጌል መስበክ ላይ መሆኑን ለማመልከትና ከራሳችን ምኞትና ስም በላይ የክርስቶስን ወንጌል ማስቀደም እንደሚገባን ለመረዳት

**የጥናት ክፍል ፡- ፊልጵስዩስ 1፡20-30**

" ይህ ናፍቆቴ ተስፋዬም ነውና በአንድ ነገር እንኳ አላፍርም ነገር ግን በህይወት ብኖር ወይም ብሞት ክርስቶስ በግልጥነት ሁሉ እንደ ወትሮው አሁን ደግሞ በስጋዬ ይከብራል ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነውና ነገር ግን በስጋ መኖር ለእኔ የሥራ ፍሬ ቢሆን ምን እንድመርጥ አላስታውቅም በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው ይህንንም ተረድቼ በእናንተ ዘንድ እንደ ገና ስለ መሆኔ፥ በእኔ መመካታችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ይበዛ ዘንድ በእምነት ታድጉና ደስ ይላችሁ ዘንድ እንድኖር ከሁላችሁም ጋር እንድቈይ አውቃለሁ ይሁን እንጂ፥ መጥቼ ባያችሁ ወይም ብርቅ በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሃይማኖት አብራችሁ እየተጋደላችሁ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ ስለ ኑሮአችሁ እሰማ ዘንድ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ ይህም ለእነርሱ የጥፋት ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፥ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና "

የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. በቁጥር 20 ላይ ጳውሎስ በአንድ ነገር እንኳ አላፍርም ያለበት ምክንያት ምንድነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. ቁጥር 21 ጳውሎስ ለኔ ሕይወት ክርስቶስ ሞት ጥቅም ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

3. ሐዋርያው ጳውሎስ የተያዘባቸው ሁለት ሃሳቦች ( የተጨነቀባቸው) ምንድን ናቸው?

ቁጥር 24 ስታነብ አስፈላጊ ነው ብሎ ያስበውስ ምንድን ነው ከሁለቱ ሃሳቦች?

ለምን ? ( ቁጥር 25-26)

4. ሐዋርያው ጳውሎስ በቁጥር 27-28 ለፊልጵስዮስ አማኞች የመከራቸው ነጥቦች ምን እንደሆነ ትረዳለህ?

ምን ማለቱ እንደሆነ በተራ ጻፉቸው እና ለውይይት ተካፋዮችህ በማብራራት አካፍላቸው፡፡

5. የቁጥር 29ን ሃሳብ ስታነብ ምን ትረዳለህ? ከቁጥር 30 ሃሳብ ጋርስ ምን ተመሳሳይነት አለው?

6. ቁጥር 20 መሰረት በሁለንተናዬ ክርስቶስ ይከበራል እንዲል ያስቻለው ምንድን ነው?

አንተስ ይህንን ስታነብ በህይወትህ እንደዚህ ለማለት ድፍረት አለህ?

7. ሐዋርያው ጳውሎስ በከባድ ችግርና መከራ ላይ እያለ ወደጌታ መሄድና ማረፍ ምርጫው መሆን ሲችል ስለቅዱሳኑ ማሰብና መጨነቁን ስትመለከት ከሐዋርያው ጳውሎስ ህይወት ምን ትምህርት ለህይወትህ ትቀስማለህ?

8. አንተስ የክርስትና ህይወትህን ስትመለከት ከራስህ ጥቅም አስቀድመህ የጌታን ቅዱሳን እንደ ጳውሎስ የምትወድና ስለእርሱ የምታስብ ነህ ለውይይት ተካፋዮችህ አካፍል።

9. ህይወትህን ስትመለከት እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ምድር በመኖሬም ሆነ በመሞቴም ጌታ ይከብራል የሚል ዓላማ እና ቁርጥ ውሳኔ አርገሃል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ከክፍሉስ ሃሳብ ከዚህ የተማርከውና እንደዚህ ያለ ቁርጥ ውሳኔ ለማድረግ እና ለመተግበር የሚያበቃ ምን ቢደረግ እንደሚገባን የተማርከውን ለውይይት ተካፋዮችህ አካፍላቸው።

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

<u>ማስታወሻ</u>

- ከዚህ ክፍል ጌታ ባስተማረህ እውነት በመነሳት ላንተምሆነ ለውይይት ተካፋዮችህ በመፀለይ ይህንን ጥናት በፀሎት ጨርስ።

“ቅድስና ለእግዚአብሔር”
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 1፡21**

**“ ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነውና ”**

## ክፍል አራት

ርዕስ ፡- በአንድ ሃሳብ መስማማት

መግቢያ ፡- ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ስለአንድነት ያስተማረውን ትምህርት በዛሬው ጥናታችን እንማራለን

ዓላማ ፡- በቤተክርስቲያን ውስጥ አንድነትን ህብረትን ለመጠበቅ በትህትና መኖር እንደሚገባ ለማስገንዘብ

**የጥናት ክፍል ፡- ፊልጵስዩስ 2፡1-4**

" በክርስቶስም አንዳች ምክር ቢሆን የፍቅር መጽናናት ቢሆን የመንፈስ ኅብረት ቢሆን ምሕረትና ርኅራኄ ቢሆኑ ደስታዬን ፈጽሙልኝ በአንድ አሳብ ተስማሙ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ "

የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. ሐዋርያው በቁጥር 1 በክርስቶስ አገኘኋቸው ብሎ የዘረዘራቸው ምን ምን ናቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. ቁጥር 2 ስታነብ ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች ምን በማድረግ ነው ደስታዬን ፈፅሙልኝ የሚላቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

3. በቁጥር 1 ላይ የተዘረዘሩት ከክርስቶስ ያገኘናቸው ነገሮች በ ቁጥር 2 ላይ ያሉትን ትዕዛዞች ለመፈፀም እንዴት ይረዶቸዋል ብለህ ታስባለህ?

4. በቁጥር 3-4 ላይ ያሉትን ትዕዛዞች እያንዳንዱን በመፃፍ የተረዳህውን በማብራራት ለውይይት ተካፋዮችህ አካፍላቸው::

5. በ “ መንፈስ አንድነት” እና በ “በአንድ ላይ በመሰብሰብ/ በመሆን” መካከል ያለውን ልዩነት በማብራራት የተረዳህውን ለውይይት ተካፋዮችህ አካፍል::

“ቅድስና ለእግዚአብሔር”

6. በቤተክርስቲያን ውስጥ የመንፈስ አንድነት በጣም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

7. ከክፍሉ ከተማርከው ለአንድነት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

8. ከሌሎች ክርስቲያን ወንድሞች ጋር በቤተክርስቲያን ያለህን ህብረት/ አንድነት ስትመለከት በቁጥር 2 ላይ የተገለጸው ዓይነት አንድነት/ህብረትን ታያለህ?

ከሌለስ ይህን አንድነት/ ህብረት ለማምጣት ምን ማድረግ ይገባል ብለህ ታስባለህ?
ካለስ ይህንን አንድነት/ ህብረት ለመጠበቅ ምን ማድረግ ይገባል ብለህ ታስባለህ ?

የክፍሉን ሃሳብ በመመልከት የመንፈስ አንድነት ለማግኘት/ ለማምጣት ከእኔ የሚጠበቀው ምንድነው ብለህ ታምናለህ?

"ቅድስና ለእግዚአብሔር"
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

<u>ማስታወሻ</u>

- ከዚህ ክፍል በተማርከው እና በተረዳኸው እውነት በመነሳት ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ፡፡

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**
**ፊልጵስዩስ 2፡3-4**
**" ... እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር**
**እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት**
**ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ ..."**

## ክፍል አምስት

ርዕስ ፡- ጌታ እየሱስ ክርስቶስን በትህትና መምሰል

መግቢያ ፡- ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ስለትህትና ያስተማረውን ትምህርት በዛሬው ጥናታችን እንማራለን

ዓላማ፡- በትህትና ክርስቶስን እየመሰልን ከሌሎች አማኞች ጋር በአንድነት መኖር እንደሚገባ ለማስተማር

### የጥነሰቱ ክፍል ፊልጵስዩስ 2፡5-11

" በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው "

የመወያያ ጥያቄዎች ፡-

1. ቁጥር 5 በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን ያለው የቱን ሃሳብ ነው?

2. ፊልጵስዮስ 2፡5-11 ስታነብ ክርስቶስ ከመጀመሪያ ጀምሮ ማን እንደሆነ/እንደነበር ትረዳለህ ?

3. ቁጥር 7 እና 8 ስታነብስ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ ያደረገባቸውን እያንዳንዱን ሃሳቦች ስታነብ ምን ትማራለህ ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

4. ራስን ባዶ አደረገ ሲል ምን ማለቱ ነው ?

______________________________________________

______________________________________________

አምላክነቱን ተወ ማለት ነው?

______________________________________________

______________________________________________

5. ቁጥር 10 እና 11 ስታነብ ከቁጥር 5 እስከ 9 ጋር ያለውን ዝምድና ምን ትረዳለህ ከዚህስ ለህይወታችን ምን ትምህርት እንወስዳለን ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

“ቅድስና ለእግዚአብሔር” ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

6. በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ምን አደረገው?

______________________________________________

______________________________________________

እየሱስ ዛሬ ያለውን ክብርና ስልጣን አብራራ?

______________________________________________

______________________________________________

7. እኛስ ጌታን ስናገለግል በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ የነበረው ሃሳብ በህይወታችን መኖሩ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ትማራለህ ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

8. ዛሬስ በቤተክርስቲያን ጌታ በሰጠን አገልግሎት ስናገለግል ይህ መሰረታዊ እውነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ትረዳለህ ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ክርስቶስን በትህትናው ለመምሰል (ራስህን ዝቅ አድርገህ ሌሎችን ለማገልገል) ምን ለማድረግ በግል ህይወትህ አሰበሃል?

______________________________________________

______________________________________________

በእግዚአብሔር ቤት መከበር የሚገኘው በምን እንደሆነ ከዚህ ክፍል ትማራለህ?

______________________________________________

______________________________________________

9. ሌላ ለህብረታችን እርስ በእርስ ላለን ግንኙነት ጠቃሚ ነው ብለህ የተማርከውን ነገር ካለ ለውይይት ተካፋዮችህ አካፍል ::

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

“ቅድስና ለእግዚአብሔር”
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

<u>ማስታወሻ</u>

- ከዚህ ክፍል በተማርከው መሠረት ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ፡፡

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 1፡6**

**“ በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን ”**

## ክፍል ስድስት

ርዕስ ፡- እንደ ብርሃን መታየት

መግቢያ ፡- ሐዋርያ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ምዕመናን ባላመኑት መካከል እንዴት መኖር እነደሚገባቸው ያስተማረውን ክፍል እንመለከታለን

ዓላማ፡- ኃጢያት በሞላበት ዓለም ያለነቀፋ በመኖር ወንጌልን ላላመኑት ማዳረስ እንዳለብን

### የጥናት ክፍል ፡- ፊልጵስዩስ 2፡12-16

" ስለዚህ ወዳጆቼ ሆይ ሁልጊዜ እንደ ታዘዛችሁ፥ በእናንተ ዘንድ በመኖሬ ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ስርቅ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለ ነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ሳታንጐራጉሩ ክፉም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ በእነርሱም መካከል የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ፥ ስለዚህም በከንቱ እንዳልሮጥሁ በከንቱም እንዳልደከምሁ በክርስቶስ ቀን የምመካበት ይሆንልኛል "

የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. ሐዋርው ጳውሎስ በቁጥር 12 ላይ የሰጣቸውን ትዕዛዝ አብራራ?

____________________

____________________

____________________

____________________

በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ ሲል ምን ማለቱ ነው?

____________________

____________________

____________________

የምትድኑት /ደህንንት በራሳችሁ ስራ ነው ማለቱ ነው?

____________________

____________________

____________________

2. የቁጥር 13 ስታነብ ከክፍሉ ሃሳብ ምን ትረዳለህ ይህንን ሃሳብ አብራራ እና የተረዳህውን ለውይይት ተካፋዮችህ አካፍል::

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ከቁጥር 12 ሃሳብ ጋር ( የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ) እንዴት ታገናኘዋለህ/ ትረዳዋለህ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

3. ቁጥር 14-15 ያለውን ሃሳብ ስትመለከት ምን ትረዳለህ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

4. በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል የክርስቲያኖች የነሱ/የእኛ ሃላፊነት ምን ማድረግ እንደሆነ ትማራለህ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

"ቅድስና ለእግዚአብሔር"

5. ከቁጥር 12 ስታነብ ለብቻህም ስትሆን ወይም ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር መንፈሳዊ ህይወትህን እንዴት መጠበቅ እንዳለብህ፤ ምን ማድረግ እንደሚገባህ፤ ለክርስትና ህይወትህ የተረዳህውን አካፍል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

6. ቁጥር 13 ስታነብ መልካም ኑሮን ለመኖር እንዴት እንደምትችል የተማርከውን ለቡድንህ አካፍል::

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

7. የራስህን ሕይወት ስታይ ከቁጥር 14-16 ያለው ዓይነት ክርስቲያናዊ ኑሮ ይታይብሃል?

ካልሆነስ ይህንንስ ለመፈጸም ምን ልታደርግ አሰበሃል ለውይይት ተካፋዮችህ አካፍላቸው።




**ማስታወሻ**

- ከዚህ ክፍል በተማርከው እና በተረዳኸው እውነት በመነሳት ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ፡፡

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 2፥13**

**" ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነው "**

## ክፍል ሰባት

ርዕስ ፡- የአገልጋይ ባህርይ

መግቢያ ፡- ሐዋርያ ጳውሎስ በአገልግሎታቸው መልካም ምሳሌነት ስላላቸው ስሉለት አገልጋዮች የጻፈውን ክፍል እንመለከታለን

ዓላማ፡- ከራሳችን ይልቅ ሌላውን ለማገልገል ራሳችንን በመስጠት የክርስቶስን ምሳሌነት የምንከተል አገልጋዮች መሆን እንዳለብን ለማስገንዘብ

**የጥናት ክፍል ፡- ፊልስዮስ 2፡17-30**

“ ነገር ግን በእምነታችሁ መሥዋዕትና አገልግሎት ተጨምሬ ሕይወቴ እንኳ ቢፈስ ደስ ብሎኛል ከሁላችሁም ጋር አብሬ ደስ ብሎኛል እናንተም ደግሞ እንዲሁ ደስ ይበላችሁ ከእኔም ጋር አብራችሁ ደስ ይበላችሁ ነገር ግን ኑሮአችሁን ሳውቅ እኔ ደግሞ ደስ እንዲለኝ ፈጥኜ ጢሞቴዎስን ልልክላችሁ በጌታ በኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ እንደ እርሱ ያለ ስለ ኑሮአችሁ በቅንነት የሚጨነቅ ማንም የለኝምና ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም ነገር ግን ልጅ ለአባቱ እንደ ሚያገለግል ከእኔ ጋር ሆኖ ለወንጌል እንደ አገለገለ መፈተኑን ታውቃላችሁ እንግዲህ እንዴት እንደምሆን ባየሁ ጊዜ እርሱን ቶሎ እንድልክ ተስፋ አደርጋለሁ ራሴ ደግሞ ግን ፈጥኜ እንድመጣ በጌታ ታምኜአለሁ ነገር ግን ወንድሜንና ከእኔ ጋር አብሮ ሠራተኛ ወታደርም የሚሆነውን የእናንተ ግን መልእክተኛ የሆነውና የሚያስፈልገኝን የሚያገለግለውን አፍሮዲጡን እንድልክላችሁ በግድ አሰባለሁ ሁላችሁን ይናፍቃልና እንደ ታመመም ስለ ሰማችሁ ይተክዛል በእውነት ታሞ ለሞት እንኳ ቀርቦ ነበርና ነገር ግን እግዚአብሔር ማረው ኀዘን በኀዘን ላይ እንዳይጨመርብኝ ለእኔ ደግሞ እንጂ ለእርሱ ብቻ አይደለም እንግዲህ እንደ ገና ስታዩት ደስ እንዲላችሁ ለእኔም ኀዘኔ እንዲቃለል በብዙ ፍጥነት እልከዋለሁ እንግዲህ በሙሉ ደስታ በጌታ ተቀበሉት እርሱን የሚመስሉትንም አክብሩአቸው በእኔ ዘንድ ካላችሁ አገልግሎት እናንተ ስለሌላችሁ የጎደለኝን እንዲፈጽም በነፍሱ ተወራርዶ ከጌታ ሥራ የተነሣ እስከ ሞት ቀርቦአልና ”

የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. ሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወቴ መስዋዕትም ቢሆን ደስ ይለኛል እንዲል ያበቃው ነገር ምንድን ነው ብለህ ትረዳለህ? ( ቁጥር 17-18)

___

___

___

2. ቁጥር 19 ስታነብ ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሊልክ ያሰበበት ምክንያት ምንድነው?

3. ጳውሎስ ስለጢሞቲዎስ የዘረዘራቸው ሃሳቦችን አብራራ? ( ቁጥር 20-22)

4. በጢሞቲዎስ ህይወት ውስጥ ፊሊ. 2፡ 3-4 ያለው ትዕዛዝ እንዴት በተግባር ላይ እንደዋለ ትረዳለህ?

5. ሐዋርያው ጳውሎስ ስለአፍሮዲጡን የሰጠውን ምስክርነት በዝርዝር አብራራ?(ቁጥር 25-30)

ሠራተኛ ወታደር ምን ማለት ነው?

ለፊልጲስዮስ ሰዎችና ለሐዋርያው ጳውሎስ የነበረው አገልግሎት ምን ነበር? (ቁጥር 25-30)

የአፍሮዲጡን ጭንቀት ምን ነበር? ( ቁጥር 26)

አፍሮዲጡን በምንስ ሁኔታ ውስጥ ነበር? ( ቁጥር 26)

6. በፊሊ. ምዕራፍ 2፡3-11 ያለው ትዕዛዝ በአፍሮዲጡን ህይወት እንዴት ተገልፆ ታያለህ?

7. ሐዋርያው ጳውሎስ አፍሮዲጡን ሊልክ ያሰበበት ምክንያት ምንድነው? (ቁጥር 28)

8. የራስህን ህይወት ከሐዋርያው ጳውሎስ፤ ከጢሞቲዎስ፤ ከአፍሮዲጡን፤ ሕይወት ጋር እንዴት ታስተያየዋለህ?

የሚጎድልህስ ምንድነው?

9. ከዚህ ክፍል ባገኘኸው ትምህርት መሠረት ወደፊትስ ምን ልታደርግ አስበሃል/ ወስነሃል?

“ቅድስና ለእግዚአብሔር”
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

<u>ማስታወሻ</u>

- ከዚህ ክፍል በተማርከው እና በተረዳኸው እውነት በመነሳት በእነዚህ ርዕሶች ላይ ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ፡፡

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 1፡6**

**“ በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን ”**

.

## ክፍል ስምንት

ርዕስ ፡- በጌታ መመካት

መግቢያ ፡-ሐዋርያ ጳውሎስ የሐሰት አስተማሪዎችን በማስመልከት የሰጠውን ማስጠንቀቂያና በራሱ ሕይወት ምሳሌነት የአማኙ ትምክህት በምን ሊሆን እንደሚገባው ያቀረበውን ሃሳብ እንመለከታለን፡፡

ዓላማ ፡- በሥጋ የምንመካበት ነገር ሁሉ ጥለን የሕይወታችን ዋና ዓላማ ጌታን በሚገባ ማወቅና እርሱንም መምሰል መሆን እንዳለበት ለመገንዘብ

**የጥናት ክፍል ፡- ፊልስዮስ 3፡1-11**

“ በቀረውስ ወንድሞቼ ሆይ በጌታ ደስ ይበላችሁ ስለ አንድ ነገር መልሼ ልጽፍላችሁ እኔን አይታክተኝም ለእናንተ ግን ደኅና ነው ከውሾች ተጠበቁ ከክፉዎችም ሠራተኞች ተጠበቁ ከሐሰተኛም መገረዝ ተጠበቁ እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና እኔ ግን በሥጋ ደግሞ የምታመንበት አለኝ። ሌላ ሰው ማንም ቢሆን በሥጋ የሚታመንበት እንዳለው ቢመስለው እኔ እበልጠዋለሁ በስምንተኛው ቀን የተገረዝሁ ከእስራኤል ትውልድ ከብንያም ወገን ከዕብራውያን ዕብራዊ ነኝ ስለ ሕግ ብትጠይቁ፥ ፈሪሳዊ ነበርሁ ስለ ቅንዓት ብትጠይቁ፥ ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ ነበርሁ፤ በሕግ ስለሚገኝ ጽድቅ ብትጠይቁ፥ ያለ ነቀፋ ነበርሁ ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት ቈጥሬዋለሁ አዎን በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ በመከራውም እንድካፈል ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ ”

የመወያያ ጥያቄዎች፡-

1. ቁጥር 1 ስታነብ ምን ትረዳለህ?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

ሐዋርያው ጳውሎስ ያለመሰልቸት ደጋግሞ መጻፍ ለምንስ አስፈለገው?

2. ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጲስዮስ አማኞች የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድነው?

እነማን ናቸው እነዚህ ሰዎች?

3. በምንባቡ መሠረት ስንት ዓይነት መገረዝ እንዳለ ትረዳለህ?

“ቅዱስ ለእግዚአብሔር”
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

ልዩነቱስ ምንድን እንደሆነ ትረዳለህ?

4. ሐዋርያው ጳውሎስ በሥጋ የሚታመንበት ብሎ ያቀረባቸው ነጥቦች ምንና ምን ናቸው?

ለምን ይመካል?

5. ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን አለኝ ብሎ የሚመካባቸውን ትምክህቶች እንደጉድፍና እንደኪሳራ ሊቆትራቸው ያስቻለው ምክንያት ምንድነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

6. እነዚህን ትምክህቶች ሐዋርያው ጳውሎስ እንደጉዳትና እንደ ኪሳራ በመቁጠሩ ያገኘው ጥቅም ምንድነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

7. ያገኘውን ጥቅምና እንደጉዳት የቆጠረው ትምክህት ስታስተያይ ምን ትመለከታለህ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

8. በቁጥር 10-11 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ከሁሉ በላይ ለማወቅና ለማግኘት የሚፈልገው ምንድነው ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ምን ማለት እንደሆነ የተረዳህውን አብራራ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

9. በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ልንመካበት/ሊያስመካን/ሊመካባቸው የሚችላቸው ነገሮች ምን ምን ይመስሉሃል በዝርዝር ፃፋቸውና ከውይይት ተካፋዮችህ ጋር ተወያይባቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

10. የምንመካባቸውን ነገሮች እንደጉድፍና እንደኪሳራ ለመቁጠር የሚያስችለውን በምንባቡ መሠረት ምን ይመስልሃል?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

11. በሥጋ መመካት የለብንም ስንል ምን ማለታችን ነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ለምንስ ይጠቅመናል/ ከውይይት ተካፋዮችህ ጋር ተወያይባቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

12. በቁጥር 10-11 መሠረት የተጻፉትን በሕይወታችን እንዲፈጸሙ ለማድረግ ምን ማድረግ ይገባናል?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

"ቅድስና ለእግዚአብሔር"
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

<u>ማስታወሻ</u>

- ከዚህ ክፍል በተማርከው እና በተረዳኸው እውነት በመነሳት በእነዚህ ርዕሶች ላይ ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ።

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 3፡8**

**" አዎን በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ "**

## ክፍል ዘጠኝ

ርዕስ ፦ ዓላማ ያለው ሩጫ

መግቢያ ፦ ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ ዋና ዓለማና ግብ ስለሆነው ነገር የጻፈውውን እንመለከታለን

ዓላማ ፦ በክርስትና የህይወት እድገት ብዙ እንደሚቀረን ለማስገንዘብ እያደግን ለመሄድ ምን ማድረግ እንዳለብን ለመረዳት

**የጥናት ክፍል ፦ ፊልጵስዩስ 3፡12 – 21**

“ አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ ወንድሞች ሆይ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ፤ በአንዳች ነገርም ልዩ አሳብ ቢኖራችሁ እግዚአብሔር ይህን ደግሞ ይገልጥላችኋል ሆኖም በደረስንበት በዚያ እንመላለስ ወንድሞች ሆይ እኔን የምትመስሉ ሁኑ እኛም እንደ ምሳሌ እንደምንሆንላችሁ፥ እንዲሁ የሚመላለሱትን ተመልከቱ ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ መጨረሻቸው ጥፋት ነው ሆዳቸው አምላካቸው ነው ክብራቸው በነውራቸው ነው አሳባቸው ምድራዊ ነው እኛ አገራችን በሰማይ ነውና ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል ”

የመወያያ ጥያቄዎች ፦

1. ሐዋርያ ጳውሎስ በቁጥር 12-14 መሰረት ሁሉን ነገር አግኝቻለሁ ብሎ ለመናገር የደፈረው ከምን የተነሳ ይመስልሃል?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

6. ከቁጥር 18-19 ስለማንና ማን ይናገራል?

   ሐዋርያ ጳውሎስ የነዚህ ሰዎችን የእኛ ልዩነት እንዴት እንደሆነ ነው የገለጸው?

7. ከቁጥር 12-13 ላይ ሐዋርያ ጳውሎስ ከተናገረው ነገር ለሕይወትህ ምን ትማራለህ?

   ክርስትና ሕይወት ሩጫህ ምን ያህል ይቀረዋል?

8. ወደፊት እንደሚገባ እንድትሄድ ከኆላ ሆኖ የሚጎትትህ ነገር በሕይወትህ አለ?

   ምን ማድረግ እንዳለብህ ተማርክ?

9. የያዝከውን የክርስትና ሩጫ በትጋት ለመጨረስ የሚጎዱ ለሎች ከክፍሉ የተማርካቸውን ሃሳቦችህን ለህብረትህ አካፍል? ( ቁጥር 17፡20-21)

10. በሕይወትህ ያንተ ግብ ምንድን ነው ?

ወደ ግብህስ ለመድረስ ምን ማድረግ ያለብህ ይመስልሃል?




<u>ማስታወሻ</u>

- ከዚህ ክፍል በተማርከው መሠረት ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ።

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 3፡20**

" እኛ አገራችን በሰማይ ነውና ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን "

## ክፍል አሥር

**ርዕስ ፦ የአማኝ ተግባር**

መግቢያ ፦ ሐዋርያ ጳውሎስ ለአማኞች ደስታቸው ጌታ እንደሆነና በምንም ነገር መጨነቅ እንደሌለባቸው የጻፈውን መልዕክት እንመለካታለን

ዓላማ ፦ አንድ አማኝ በህይወቱ በተጨነቀና ባዘነ ግዜ ወደ ጌታ በፀሎትና በምስጋና ማቅረብ እንዳለበትና ለመረዳት ደስታው በጌታው ላይ ብቻ መሆኑን ለመገንዘብ

### የጥናት ክፍል ፦ ፊልጵስዩስ 4፡1 – 7

“ ስለዚህ የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ ደስታዬና አክሊሌ የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ እንዲሁ በጌታ ቁሙ ወዳጆች ሆይ በአንድ አሳብ በጌታ እንዲስማሙ ኤዎድያንን እመክራለሁ ሲንጤኪንንም እመክራለሁ አንተም ደግሞ በሥራዬ አብረህ የተጠመድህ እውነተኛ ሆይ እንድታግዛቸው እለምንሃለሁ ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት ከቀሌምንጦስና ደግሞ ከእኔ ጋር አብረው ከሠሩት ከሌሎቹ ጋር በወንጌል ከእኔ ጋር አብረው ተጋድለዋልና ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ ገርነታችሁ ለሰው ሁሉ ይታወቅ ጌታ ቅርብ ነው በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል ”

የመወያያ ጥያቄዎች ፦

1. ቁጥር 1 ስታነብ ሐዋርያ ጳውሎስ ለፊልጲስዮስ አማኞች ያለው አመለካከት እንዴት ነው?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

2. ኤዋድያና ሲንጢኪ እነማን ናቸው?

________________________________________________

________________________________________________

በመሃላቸው የተፈጠረውስ ችግር ምንድን ነው?

________________________________________________

________________________________________________

3. ሐዋርያ ጳውሎስ ታማኝ ጎደኛውን በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን እንዲያደርግ ነው የሚጽፍለት?

4. በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ችግር እንኳን ቢኖር ምን እንዲያደርጉ ነው የሚመክራቸው?

5. ቁጥር 4 በጌታ ደስ መሰኘት ምን ማለት ነው? አብራራ

6. ቁጥር 5-6 ምን እንዲያደርጉ ነው የሚመክራቸው?

   የተረዳኸውን ነጥቦቹን በዝርዝር ፃፋቸው፤ እነዚህን ቢያድርጉስ ውጤቱ ምን የሚሆን ይመስልሃል?

7. ቁ.5 ሐዋርያ ጳውሎስ ገርነታችሁ(ደግነታችሁ) ለሰው ሁሉ የታወቀ ይሁን ሲል ምን ማለቱ ነው?

   እንዴት ነው ሊታወቅስ የሚችለው? ምን ብናደርግ?

8. ቁጥር 6 ስታነብ ሳንጨነቅ በምስጋና ማቅረብ ይቻል ይመስልሃል?

______________________________________________

______________________________________________

አትጨነቁ ሲልስ ምን ማለቱ እንደሆነ ትረዳለህ ?

______________________________________________

______________________________________________

9. ቁጥረ 7 ስታነብ መጥፎና የሚያሳዝን ሁኔታ ሲገጥመን በቅድሚያ መጠበቅ የሚያስፈልገን ምናችንን እንደሆነ ትማራለህ?

______________________________________________

______________________________________________

አእምሮአችንና ልባችን በእግዚአብሔር ሰላም መጠበቁ ጥቅሙ ምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

10. በቁጥር 5 ላይ ጌታ ሊመጣ ቀርቦል (ጌታ ቅርብ ነው)ማለቱ ለምን አሰፈልጎት ነው?

______________________________________________

______________________________________________

የመምጣቱ መቅረብስ ከቁጥር 5-7 ጋር ምን ግንኙነት አለው ብለህ ታስባለህ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

<u>ማስታወሻ</u>

- ከዚህ ክፍል በተማርከው መሠረት ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ።

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 4፡4**

**“ ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ ”**

## ክፍል አሥራ አንድ

**ርዕስ ፡- የሰላም ምስጢር**

መግቢያ ፡- ሐዋርያ ጳውሎስ ለፊሊጲስዮስ አማኞች በሃሳባቸውና በድርጊታቸው ሁሉ ማድረግ የሚገባቸውን ዋነኛው ተቀዳሚ ነገር የጻፈላቸውን እንመለካታለን

ዓላማ፡- የእግዚአብሔር ሰላም ከእኛ ጋር እንዴት ሊሆን እንደሚችል ለመረዳት

**የጥናት ክፍል ፡- ፊልስዮስ 4፡8 – 9**

“ በቀረውስ ወንድሞች ሆይ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን እነዚህን አስቡ ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል ”

የመወያያ ጥያቄዎች ፡-

1. ሐዋርያ ጳውሎስ ለፊሊጲሲዮስ ሰዎች የሰጣቸው ሁለት ዋና ቁልፍ ምክሮች ምንድናቸው?

2. በአእምሮአቸው እንዲያስቡ (.....እነዚህን አስቡ )የነገራቸው ነጥቦች ምን ምን እንደሆኑ ከክፍሉ ሃሳብ ትረዳለህ? እነዚህንም ነጥቦች በዝርዝር ምን ማለት እንደሆኑ በመጻፍ አብራራቸው፡፡ -- ከውይይት ተካፋዮችህ ጋር ምን ማለት እንደሆነ አንድ ባንድ ተወያይባቸው ፡፡

እንዴት ነው እነዚህ ነገሮች ማሰብ ማለት?

3. እንዲያደርጉስ (እነዚህን አድርጉ)የሚያሳስባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

4. እነዚህ ሁለት ነገሮች (ማሰብና / ማድረግ) እንደ ቃሉ ቢያደርጉ ውጤት ምን እንደሚሆን ትረዳለህ/ትማራለህ?

5. ከእነዚህስ ሁለቱ ነገሮች አንዱን ብቻ ብናደርግ የጥያቄ አራት መልስ በህይወታችን ይሰራለታል ብለህ ታምናለህ?

“ቅድስና ለእግዚአብሔር”
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

6. ምን ማለቱ እንደሆነ ትረዳለህ “ የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል ” ሲል?

ጌታ በውስጣችን ለዘላለም ይኖራል ከሚለው ሃሳብስ ጋርስ እንዴት ታስታርቀዋለህ?

7. በስራህም ሆነ በዕለት ኑሮህ አብዛኛውን ጊዜ የምታስበውና የምታሰላስለው ስለምንድን ነው?

ቁጥር 8-9 መሠረት ካሁን ጀምሮ ምን ማድረግ እንዳለብህ ተምረሃል?

8. ማሰብና ማድረግ ውጤታቸው በምንባቡ መሠረት ምንድነው ብለህ ታስባለህ?

**ማስታወሻ**

- ከዚህ ክፍል በተማርከው መሠረት ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ፡፡

“ቅድስና ለእግዚአብሔር”
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 4፡8**

“ በቀረውስ ወንድሞች ሆይ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፤ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፤ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፤ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፤ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፤ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፤ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን እነዚህን አስቡ ”

## ክፍል አሥራ ሁለት

ርዕስ፡- ልብ የሞላው ስጦታ

መግቢያ፡- ሐዋርያ ጳውሎስ ለፊሊጲስዮስ ቤተክርስቲያን ስለተላከው ስጦታ የተሰማውን ደስታና ምሥጋና እንመለከታለን

ዓላማ፡- በገንዘባችን ወይም ባለን ነገር ለወንጌል ስራ ማስፋፊያ መደገፍ እንዳለብን በዚሁ አገልግሎት የሚያገለግሉትን መረዳት እንደሚያስፈልገንና ባለን ነገር ደስተኞች መሆን እንዳለብን ለመረዳት

### የጥናት ክፍል ፡- ፊልስዮስ 4፡10 – 19

“ ነገር ግን አሁን ከጊዜ በኋላ ስለ እኔ እንደ ገና ልታስቡ ስለ ጀመራችሁ በጌታ እጅግ ደስ ይለኛል ጊዜ አጣችሁ እንጂ ማሰብስ ታስቡ ነበር ይህን ስል ስለ ጉድለት አልልም የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁና መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ ሆኖም በመከራዬ ከእኔ ጋር ስለ ተካፈላችሁ መልካም አደረጋችሁ የፊልጵስዩስ ሰዎች ሆይ፥ ወንጌል በመጀመሪያ ሲሰበክ ከመቄዶንያ በወጣሁ ጊዜ ከእናንተ ብቻ በቀር ሌላ ቤተ ክርስቲያን በመስጠትና በመቀበል ስሌት ከእኔ ጋር እንዳልተካፈለች እናንተ ደግሞ ታውቃላችሁ በተሰሎንቄ እንኳ ሳለሁ አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ ያስፈለገኝን ሰዳችሁልኝ ነበርና በስሌታችሁ የሚበዛውን ፍሬ እንጂ ስጦታውን ፈላጊ አይደለሁም ነገር ግን ሁሉ አለኝ ይበዛልኝማል የመዓዛ ሽታና የተወደደ መሥዋዕት የሚሆነውን ለእግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን ስጦታችሁን ከአፍሮዲጡ ተቀብዬ ተሞልቼአለሁ አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል ”

የመወያያ ጥያቄዎች ፡-

1. ቁጥር 10 ጳውሎስ ከፍተኛ ደስታ የተሰማው በምን ምክንያት ነው?

2. ቁጥር 11 ላይ ያለኝ ይበቃኛል ማለት ተምሬአለሁ ሲል ምን ማለቱ ነው?

3. በቁጥር 12 ላይ ያሉትን ነገሮች ለማለት ያስቻለው ምክንያት ምንድነው ትላለህ?

የቻለውስ እንዴት ነው በምን ኃይል (ቁጥር 13) ?

4. የፊልጲሲዮስ አማኞች ለሐዋርያው ጳውሎስ ምን ያደርጉለት ነበር (ቁጥር 14-16)?

5. በቁጥር 11, 17 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ምን እንዲያስተውሉ ነው የሚናገራቸው እየደጋገመ?

"ቅድስና ለእግዚአብሔር" ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

6. የተላከለት ስጦታ መጠኑ ምን ያህል ነው ?

ስጦታውን ከምን ጋር ያመሳስለዋል? ሊያመሳስልበት ያስቻለው ምክንያትስ ምንድን ነው?

7. ቁጥር 11-12 ላይ ስትመለከት ስለጳውሎስ ምን ትማራለህ?

አንተስ በእነዚህ ሁሉ ነገሮች ውስጥ ብታለፍ ጸንተህ መቆም ትችላለህ?

ስለዚህ ምን ማድረግ እንዳለብህ ታስባለህ ወደዚህ ደረጃ ለመድረስ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

8. ከፊሊጲሲዮስ አማኞች በቁጥር 14-15 ስትመለከት በህይወትህ ወይም በቤተክርስቲያን ይሄንን አይነት ባህርይ ታያለህ?

______________________________________________

______________________________________________

ካልሆነስ/ከሆነስ ለምን ይመስልሃል? ታዲያ ምን ማድረግ አለብን ብለህ ታስባለህ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

<u>**ማስታወሻ**</u>

- ከዚህ ክፍል በተማርከው መሠረት ለግል ህይወትህ ለቤተሰብህ ለቤተክርስቲያን እና ለውይይት ተካፋዮችህ ፀሎት በማድረግ የዛሬውን ጥናት በፀሎት ጨርስ፡፡

“ቅድስና ለእግዚአብሔር”
ዘፀ 28:36 ዘፀ 39:30

**በቃል የሚጠና የሳምንቱ ጥቅስ**

**ፊልጵስዩስ 4፡12-13**

“ መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ ”